# ትግላችን መመራት ያለበት በማን ነው?
# በወያኔና በውጭ ቅጥረኞች ወይስ በሀቀኛ ታጋዮች?

ግርማ አጋ

የጸረ ወያኔ ትግል እየተጠናከረ በመጣ ቁጥር ያንን ኃይል የሚከፋፍልና የሚያዳክም ክፍልና ግለሰቦች እየተነሱ የተቃዋሚውን ጎራ ሲያዳክሙ በየጊዜው ተስተውሏል። በተለይ በውጭ አገር ማንም ሰው ሀሳቡን መስጠትና መግለጽ በሚችልበት ሁኔታ ሁሉም አዋቂ ሁሉም መሪ ልሁን እያለ ያለቦታው እየገባ ሲያንቧችርና ሲፈተፍት ተስተውሏል። በተለያዩ ጊዜ ከሚታገለው ክፍል በላይ የሚቆረቆሩና የሚሰሩ መስለው በመታየትና በተለያዩ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ወይም እንቅስቃሴ ክፍል ውስጥ ከገቡ በኋላ በረቀቀ መንገድ ትግሉ ላይ ቀዝቀዛ ውሃ እየቸለሱና የትግሉን አቅጣጫ እያሳቱ ትግሉ የአንድ ሰሞን ትግል ብቻ ሆኖ ይቀራል። እነዚሁ ኃይሎች ደግሞ ሌላ ጊዜ መልካቸውን ቀይረው ሌላ ባርኔጣ አድርገው ያንኑ የማዳከምና አቅጣጫ የማይስቀየር ስራውን ይደጋግማሉ። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት በፈረደበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ወይም ወያኔን በሚታገለው ኃይል ስም ነው።

እነዚህ ትግሉን ተቆጣጥረው አቅጣጫ ለማስቀየር የሚሰሩ ግለሰቦችና ቡድኖች አንድም በወያኔ ቀጥተኛ ትእዛዝ ለሆዳቸውና ለጥቅማቸው አድረው አሊያም በውጭ ኃይሎች ተገዝተው የታዘዙትን የሚፈጽሙ ናቸው። በአንድ ሙያ ለምሳሌ በኪነት የታወቁ፣ በስፓርት የታወቁ፣ ወይም በተማሩበት ሙያ የታወቁ ግለሰቦችና በንግድ መስክ የተሰማሩ፣ ምን እንደሚሰሩ የማይታወቅ ሆኖም የተደላደለ ኑሮ የሚኖሩ ግለሰቦችን ያካተተ ሲሆን በቅድሚያ እነዚያ ሰዎች ወደ መድረክ የሚመጡበትን መድረክ ተመቻችቶና ባሉበት አካባቢ ታዋቂ እንዲሆኑ ይደረጋል። ከዚያም በአንድ ሰሞን የተከሰተን ድርጊት አስመልክቶ አስተያየታቸውን በሚዲያ እንዲሰጡ ይደረጋል። ጥቂት ቆይቶ የዚህ የዚህ አስተባባሪ ኮሚቴ ወይም አካል መሆናቸውን ይገለጻል። ማን እንደመረጣቸው ግን አይታወቅም። እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያሉ ግለሰቦች ናቸው በጸረ ወያኔ ትግል ውስጥ እየገቡ የማፈራረስ፣ ግራ የማጋባትና አቅጣጫ የማስቀየር ተግባር ሲፈጽሙብን የኖሩት። በዚህ ደግሞ የወያኔ ዕድሜ ተራዘመ። ኅበዝ ልብ ልንል ይገባል። አንዴ ባለማወቅ መታለል እሺ ሁሌ ሲደጋገም እየተቀበሉ መኖር ግን በጣም ከባድ ስህተት ነው።

ሐቀኛ ታጋዮችን ስም በማጥፋትና በማንኳሰስ እነርሱ ለውጥ የሚያመጣ ክፍል መስለው የተሰራውን ስራ ሁሉ ሲያንኳስሱ፣ በረዢሙ የትግል ዓመታት የት እንደነበሩ ሳይታወቅ በአንድ ቀን ጀምበር ብቅ ብለው መሪ የሚሆኑት ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬና ማንነታቸውን የማወቅ ተግባር ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። የወያኔ አባል ሆነው ስንት ወንጀል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሲፈጽሙ ቆይተው በአንድ ቀን ጀምበር "ጀግና" ይባልሉናል። እነርሱን ደግሞ የሚያስተናግዱት እነዚሁ ትግሉን ሲያዳክሙና ሲከፋፍሉ የነበሩት እንደ እርጎ ዝንብ በየቦታው ጥልቅ የሚሉት ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸው። እውነቱን መናገርና እነዚህን ግለሰቦች ማጋለጥ እንደ ወንጀል ተቀጥሮ አንዳንድ ሰዎች ሲጽፉና ሲኮንኑ ሰሞኑን እየተስተዋለ ነው።

በጸረ ወያኔ ትግል ውስጥ ለረጂም ጊዜ የደብተራው ድኀረ ገጽ፣ የኢትዮ ላየን፣ የአሲምባና ማኀደር ድኀረ ገጾች ከፍተኛውንና ቀዳሚ ሚና ይይዛሉ። ያለፍርሃት ባንዳውን ባንዳ፣ ከሃዲውን ከሃዲ፣ አንጃውን አንጃ ብለው አጋልጠዋል። የወያኔን ወንጀልና ደባ አሳውቀዋል። ጠቃሚ መረጃዎችንና ዜናዎችን አቅርበዋል። በፍርሃትና በጥቅም ግን ወደ ኋላ ያሉበት ወቅት አልታየም። ያ በታሪክ ውስጥ ሲያስመሰግናቸውና ሲያኮራቸው እንጂ ዛሬ ትግሉን ሊነጥቁና ለወያኔ ሊገብሩ የሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖች በእነዚህ ድኀረ ገጾች ላይ የጥፉት ዒላማቸውን ማነጣጠራቸው የድኅረ ገጾቹን ጠንካራ አቂም እንደማያዛንፍ እናምናለን። በዚህ ውጭ ባለነው አገር ደግሞ የአንድን ግለሰብ ወይም አካል ክፍል ማስፈራራትም ሆነ ስም ማጥፋት በህግ ሊያስጠይቅ የሚችል መሆኑን መረዳት አለባቸው።

ትላንት በአንድነት ሆኖ ሲታገል ሲጮኽ የነበረውን ክፍል የበታተኑት ኃይሎች ዛሬ ጸረ ወያኔ አጀንዳችን ማስቀየርና እነርሱ በሚፈልጉት አቅጣጫ መምራት ነው። ትላንት ከወያኔ ጋር ሲሞዳሞዱ፣ የአላሙዲን ጋሻ ጃግሬ ሆነው ሁሉን በሆዱ ለመግዛት ሲራወጡ፣ እነ ሰዬ አብርሃ ዋሽንግተን ሲመጡ የጀግና አቀባበልና አታሞ ሲመቱ የነበሩ ግለሰቦች፣ የቅንጅት መሪዎች ሲታሰሩ የአገሩም የውጭውም የትግል መሪዎች እኛ ነን ብለው ራሳቸውን የሾሙ ግለሰቦች፣ ከነ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሀቅ ጋር በየሆቴሉ ሲዶልቱ የነበሩ ግለሰቦች፣ በየወያኔ ኤምባሲው ስራ ሲያመለክቱ የነበሩና አገር ቤት ኤንቨስት እያደረጉ ያሉ ሰዎች እንደ አሸን በፈለፈሏቸው ድኅረ ገጾች፣ እንደ (ETN) ቴሌቪዥን ጣቢያ፣በከረንት አፌርስ፣ (VEDR) ፓልቶክ ክፍሎችና በተለያዩ ሬዲዮ ጣቢያዎቻ.ው አማካኝነት ከወያኔና ከውጭ ኃይል የተሰጣቸውን የቤት ስራ በመስራት ላይ

ይገኛሉ:: በአገር ቤት የሚካሄደው ሀቀኛ ትግል የሚንቀሳቀስበት የገንዘብ እርዳታ እጅግ በሚያስፈልግበት ጊዜ እነዚህ ክፍሎች ያለምንም የገንዘብ ችግር በከፍተኛ ወጪ ይካሄዳሉ:: ሕዝባዊ ስብሰባዎች ተጠርተው የሕዝብ ድጋፍ ሲሰጥ አናይም፣ የገንዘብ መዋጮ ሲደረግ አናይም ታዲያ የሚንቀሳቀሱበት ገንዘብ ከየት ተገኘ? ያጠያይቃል::- (ETN) ከየት መጣ ሳይባል ከዓመት በፊት የተሟላ የቴሌቪዥን ጣቢያ ያውም 24 ሰዓት 365 ቀን በሚያስተላልፍበት ሁኔታ ከሰማይ ወርዶ እነ ታማኝ ሲያንቧቹሩበት አዕምሮአችን ውስጥ ጥያቄ ሊያንቃጭል ይገባው ነበር! የቅንጅት መሪዎች ሲታሰሩ "ቅንጅት እኛ ነን" ብለው የነበሩት ድምጻቸውን አጥፍተው ዛሬ እነ ብርሃነ መዋ የቴሌቭዥን ጣቢያው ኃላፊ ሆነው የውስጥ ሰራቸውን እየሰሩ ናቸው:: እነዚያ የውጭውን ትግል ሲያዳክሙ የነበሩ ሰዎች ዛሬ ጥቂት አዳዲስ ሰዎችን ከፊት አስቀድመው ከየቦታው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ:: ዛሬም አመጣጣቸው ግልጽ ነው:: ትግሉን ከተቃዋሚው ላይ ነጥቀው በውጭ ኃይሎችና በወያኔ የረቀቀ የተንኮል ስራቸውን ለመስራት ነው:: የወያኔ 52 ገጽ ማንዋል ከ 50 ሚሊዮን ዶላር ጋር ስራውን በተግባር እያየነው ነው:: ለዚህ ደግሞ ድራማው የተሳካ እንዲሆን ተዋንያኑ ከጳጳሱ በላይ ቄሱ ሆነው መገኘት አለባቸው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እኮ የወያኔን ቡድን አሽቀንጥሮ ጥሎ ዲሞክራሲያው ሰርዓት መገንባትና ሕዝብ የመረጠው መንግሥት ማቋቋም ነው:: እነርሱ የሚሰጡንን አጀንዳ አንጠ ልጥለን መሮጥና መጃጃል የለብንም:: ማንም ሰው ያለ አግባብ መታሰር የለበትም ትክክለኛ መርሆ ነው:: በዚያም መሰረት ሁሉም የፖለቲካ እስረኛ ይፈታ መባል እንጂ ብርቱካንና ቴዲ ብቻ እንዲፈቱ መታገል ትክክል አይደለም:: በኢትዮጵያ ያሉ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ስንል ያለ ፍርድ ታስረዋል ፍትሕ አጥተዋል ማለታችን ስለሆነ የሕዝብ ጥያቄ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ብርቱካን ትፈታ አይደለም:: ሁሉም ለቤተሰቡ ሁሉም ለሀገሩ እኩል ስለሆነ ትግላችን ሁሉንም ለማስፈታት ነው:: በትግሉም አንጻር ብንመለከት ብርቱካን የመሰረተችው ፓርቲ መሪ ስለሆነች ፓርቲዋ ሊጮህና ሊታገል ይገባዋል:: አጀንዳችን ተነጥቆ ትግሉ ለአንዲት ግለሰብ መፈታት ብቻ መሆን የለበትም:: ከዚህ ቀደምም በእነ ልደቱ አያሌውና ደጋፊዎቹ አማካኝነት የወያኔን አጀንዳ ይዘን የሮጥነው ይበቃል:: ዛሬም ተመሳሳይ ድራማ እንዳለ ይታወቃል:: ያውም የተቀነባበረ! ደግሞም ነገ እናየዋለን:: በኒዮርክ ነዋሪ የሆኑ አንድ ግለሰብና በለንደን የሚኖሩ በጸረ ወያኔ ትግል ይታወቁ የነበሩ አንድ ግለሰብ የሰሞኑ አባባል ግን ብርቱካን ካልተፈታች የኢትዮጵያ ምፅዓት የደረሰ አስመስለው እያቀረቡት ነው:: ብርቱካንን መደገፍ መብታቸው ነው:: ሚዛናዊ አለማድረጋቸው ግን ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል:: ሀሳብን መግለጽ በሚቻልበት አገር በሌሎች ድኅረ ገጾች ላይ የዘመቱት የማስፈራሪያና ስም የማጥፋት ተግባርም መስመሩን ማለፉን ሊረዱት ይገባል:: ብርቱካን ትታሰር የሚል የለም:: አምና እና ከዚያ በፊት በቅንጅት ላይ የፈጸመችው አፍራሽ ተግባር ደግሞ የሚረሳ አለመሆኑን ልትረዱት ይገባል:: የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም ተብሎ የለም:: ሌላው የቺካጎ ነዋሪ ግርማ ካሣ ደግሞ ስማችንን ቀይረን "ብርቱካን ሚዴቅሳ" ሆናል ይሉናል:: እናውቅዎታለን ግርማ ካሣ:: "ለማያውቁሽ ታጠኝ" አሉ:: እርሰዎ ስምዎን ቀይረው ብርቱካን ሚዲቅሳ መባል ይችላሉ ወይዘሪት ወይም ወይዘሮ ብንልዎ እንዳይከፋዎ እንጂ ስምዎን የመረጡት እርስዎ ነዎት:: እኔም ሆንኩ ሌላው ኢትዮጵያዊ ግን ስሙን አይቀይርም:: ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል አሉ ወዴት ወዴት ግርማ ካሣ::

ጸረ ወያኔ ትግላችን ኢትዮጵያን ማዳን እንጂ ለአንድ ግለሰብ መጮህ አይደለም:: አጀንዳችንን ቀምታችሁ ከምታውቁት ቦታ ባገኛችሁት የገንዘብ መጠንና በጠላት ኃይል ተመክታችሁ ሕዝብን ግራ ማጋባታችሁ ጊዜያዊ ነው:: የዲሲና የለንደን ከበሮአችሁ የሚያደነቁረን ለጊዜው ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ማ ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል:: የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ሁሉም ይታያል:: የዛሬው ድራማ ሲያበቃ ነገ "በትግላችን አስፈታን" ተነገወዲያ በወያኔ 2010 ምርጫ ይህን ያህል ድምጽ አገኘን ተብሎ ወያኔን ለማጀብ የተጀመረው እሩጫ የትም አይደርስ:: እነ ኮማንደር ብር አሁንም በ 500 ዶላር መዋጮ ነጻ ሊያወጡን አይደል! ሁሉንም ለማየት የዚያ ሰው ይበለን::  ትግሉን ለመከፋፈልና አቅጣጫ ለማስቀየር እየተራወጣችሁ ያላችሁት አላርፍም ካላችሁ ከነ ማስረጃው ሁላችሁንም በስምና በተግባራችሁ ማጋለጥ ይቻላል:: የሕዝብን አስተያየትና ዜና በነጻነት የሚያቀርቡ ነጻ የድኅረ ገጾች ላይ የሚካሄደው ማንኛውም አፍራሽ ቅስቀሳ መቆም አለበት:: ከጸረ ወያኔ ትግል አጀንዳችን ሳለመቀየርና የሁላችሁንም ጊዜ በዚያ ላይ ማጥፋት ባለመፈለግ በዚሁ ይብቃ እላለሁ:: ጸረ ወያኔ ትግላችን ይቀጥላል::

የወያኔና የውጭ ኃይል ቅጥረኞች ሴራ ይከሽፋል!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል!